


# ውሳኔ


ድርሰት፡ ኡሩሱላ ናፍላ
የምስል ዝግጅት፡ ሹሲ ማሊንዲ
ትርጉም፡ ናትናኤል ወርቁ

©ነሐሴ 2012 የአዘጋጁ መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

ታተመ፡ በይሁን የማስታወቂያ ሥራ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር፡ +251-921-45-44-42
ኢሜል፡- wnati00@gmail.com
https://t.m https://t.me/melkamteret




በመንደራችን ውስጥ ብዙ ችግሮች ነበሩብን፡፡ ከብቸኛዋ ቧንቧችን ውሃ ለመቅዳት ለሰዓታት ረጅም ሰልፎችን እንሰለፍ ነበር፡፡




በሰዎች የሚቸረንን የምግብ እርዳታ እንጠብቅ ነበር።




በሌቦች እንዳንዘረፍ ቤታችንን በጊዜ እንዘጋለን።




በችግር ምክንያት ብዙ ልጆች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ።




ሴት ልጆች ወደ ሌሎች መንደሮች በመሄድ በሰው ቤት ተቀጥረው ለመስራት ይገደዳሉ፡፡





ብዙ ወጣት ልጆች ካለምንም ሥራ ከተማውን ሲያስሱ ይውላሉ። እድለኞቹ ደግሞ በሰዎች እርሻ ላይ ተቀጥረው ይሠራሉ።




ንፋስ ሲነፍስ አላግባብ የተጣሉ ወረቀቶች ዛፎችንና አጥሮችን ያለብሷቸዋል።




በግዴለሽነት የተጣሉ ሰባራ ጠርሙሶች የሰዎችን እግሮች ይቆርጣሉ።




አንድ ቀን የከፋ ችግር ገጠመን፡፡
አንዱና ብቸኛው የውሃ ጉድጓዳችን
ተሚጢ ማከማቻው ባዶ ሆነ፡፡




አባቴ በየቤቱ እየሄደ የመንደሩን ሰዎች ስብሰባ ጠራ።



የመንደሩ ሰዎች በአካባቢያችን በሚገኘው ዛፍ ስር ተሰብስበው መወያየት ጀመሩ።




አባቴ ብድግ ብሎ “ችግሮቻችንን ለመቅረፍ በጋራ መሥራት ይኖርብናል” አለ።




የስምንት አመቱ አቡቲ በተቀመጠበት የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ እንዳለ “እኔ በፅዳት ሥራ ማገዝ እችላለሁ አለ።”



አንዷ ጎረቤታችን “እኔ የጓሮ አትክልቶችን መትከል እችላለሁ፣ ሴቶች እህቶቼም ያግዙኛል” አለች፡፡



ሌላ ሰው ተነሳና “ወንዶቹ የውሃ ጉድጓድ እንቆፍራለን” አለ፡፡




በመጨረሻው ሁላችንም በአንድ ድምፅ “ህይወታችንን መለወጥ አለብን” ብለን ጮኽን። ከዛን ቀን ጀምሮ ሁላችንም ችግሮቻችንን ለመቅረፍ በጋራ መሥራት ጀመርን።